# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 11-20/2021 የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ከኦክቶበር 21-31/2021 የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ መጽሄት

ኦክቶበር 2021

አዲስ አበባ

ማውጫ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　ገፅ


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........................................................ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ................ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት............................... 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ............................... 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር .................................................................................................... 4

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ.................................................................... 5

በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ............................................................................... 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........................... 5

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው .......................................................... 6

ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........................................................................................... 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2021 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........ 6

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ .................................................. 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........................................................................................................ 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........................................................................................................ 8


## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ለደመና መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት የተሻለ ገፅታ ነበራቸዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በምዕራብ አማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብና በጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማና በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች በተጠቀሱት ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ ይሁን እንጂ የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከእለት ወደ ዕለት አይሎ በመስተዋሉ በአንዳንድ የመካከለኛዉና ደቡብ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት በነዚህ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በደብረብርሃን 1.8፣ በእነዋሪ 3.8 እና በባሌ ሮቤ 3.8 በድግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በጥቂት የሰሜን ጎንደር፣ አገዉ አዊ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በሸካና ቤንች ማጂ፣ በጉጂና ባሌ ዞኖች ላይ ከ25-73 ሚሜ የሚደርስ ከ4-6 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በምዕራብ ጎጃም፣ በደቡብ ጎንደር፣ በሆሮ ጉዱሩ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ፣ በአርሲ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በቦረና፣ ከአፋር ክልል በጥቂት የዞን 01፣ በፋፈንና በደገሃቡር እንዲሁም በፊቅ፣ አፍዴርና ሊበን፣ በአብዛኛዎቹ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እና በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ5-25 ሚሜ. ከ3 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፣ በምዕራብ ወለጋና ጉጂ ጥቂት ቦታዎች፣ በሰሜን ጎንደር ምዕራባዊ ክፍል፣ በአንዳንድ የሸካ፣ ቤንች ማጂ፣ ጋሞና ጎፋ እንዲሁም የአፋር ክልል ዞን 01 ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር የሁለተኛ አስር ቀናት የበጋው ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በጥቂት የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረ ቢሆንም፤ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋ እርጥበት እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርናሚቲዎሮሎጂመረጃዎችያመለክታሉ። በተጨማሪም በምስራቅ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎችም የተለያየ መጠን ያለው እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ በአጠቃላይ ባሳለፍናቸው የኦክቶበር ሁለተኛ አስር ቀናት የተስተዋለው የአየር ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የግብርና እንቅስቃሴ ላይ የተለያየ ተጽዕኖ እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል። በተለይም ደረቅ ሆነው በሰነበቱት ጥቂት የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለደረሱና በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች ደረቅና ነፋሻማ የነበረው የአየር ሁኔታ አዎንታዊ ሚና የነበረው ቢሆንም፤ በሌላ መልኩ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ፣ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎቸ ላይ የነበረው እርጥበታማ ሁኔታ ቀደም ብለው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች ገንቢ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተወሰነ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዘር ለመዝራትና እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደርች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ኢ.ኤ.አ 11-21 ኦክቶብር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በከፊል የምእራብ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛዉ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛዉና የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌዳዋ፣ መካከለኛዉ ዋቤሸበሌ እንዲሁም የላይኛውና የታችኛዉ አባይ ተፋሰሶች ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ አግኝተዋል። በተጨማሪም የታችኛው ተከዜ፣ የላይኛዉ አባይ፣ አብዛኛው የላይኛዉ ኦሞጊቤ፣ የታችኛዉ ገናሌዳዋ፣ እና በጥቂት የላይኛዉና የመካከለኛዉ ዋቤሸበሌ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውላል። (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2021 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት የበጋዉ ደረቅ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚያመዝንና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅና ደቡብ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብና በደቡባዊው አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን እንደሚኖርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የማግኘት እድል ሊኖራቸዉ ይችላል፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ዞኖች <u>ምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ አርሲ፤ የጉጂ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ የአሶሳ ዞኖች፤ የሲዳማና የጋምቤላ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የቤንች ማጂና ሸካ፤ የጌዲዮ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ከፋፊንና ከሲቲ ዞኖች በስተቀር በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉዱሩና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲና ባሌ፣ ጥቂት የቦረና ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የባህርዳር ዙሪያ፤ አገዉ አዊ፤ ምዕራብ ጎጃም ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የወላይታ፣ የከፋ፣ የዳዉሮ፣ ደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በትንበያው እንደተገለፀው በሚቀጥለው የኦክቶበር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በደቡብ ምዕራብና በደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘዉ እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች ለመጠጥ ውሃ ቅርቦት መሟላትና ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ መሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጠርላቸዋል፡፡ እንዲሁም ሁለተኛ

የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች አዲስ ለተዘሩም ሆነ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸው የሚያስፈልጋቸው የውኃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የውኃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አወንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማችት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል በሰሜናዊው አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእድገት ጊዜያቸውን እየጨረሱ ላሉና ተጨማሪ የውሃ አቅርቦት ለማይፈልጉ ሰብሎች እንዲሁም የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ ዝግጁ የሆኑ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፣ ከደረቃማው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንካራ ሊሆንና የውርጭ ክስተትንም በአንዳንድ አካባቢዎች ሊያስከትል ስለሚችል ይህም ሁኔታ በተለይም በአበባና ፍሬ በመሙላት ላይ ያሉ ሰብሎችን ሊጎዳ ስለሚችል አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲችሉ የግብርና ባለሙያዎች ቅርብ ክትትልና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ በሚገኙ በመካከለኛውና በታችኛው የተፋሰስ ክፍል ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ትንበያው ይጠቁማል። በዚህ መሰረት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ በመካከለኛውና በታችኛዉ አሞጊቤ፣ በስምጥሸለቆ፣ በገናሌዳዋ፣ በዋቢሸበሌ፣ በአባይ እና በጥቂት በታችኛው ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ እንደ ሚኖራቸዉ ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በተለይም ለዋቢሸበሌ፣ ለኦጋዴንና ለታችኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች የሚገኘው እርጥበት ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ፤ የተፋሰሶቹ የእርጥበት ሁኔታ የተሻለ እንደሚሆን ይጠበቃል። በመሆኑም የውሃ መገኘት ዘለቄታ እንዲኖረው በተለያየ መንገድ የዝናብ ውሃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነዉ ይቆያሉ፡፡